የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሰላም ሚኒስቴር

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት /2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የሰላም ሚኒስቴር

# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የሰላም ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የሰላም ሚኒስቴር የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**የገቢ ሂሳብ፤**

1. በሰኔ/2011 በጀት ዓመት መጨረሻ በገቢ ሂሳብ ሪፖርትና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መካከል የብር 1,164,951.45 ልዩነት ተገኝቷል፡፡
2. ከቤት አበል ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ ግብር በድምሩ ብር 20,700.00 ተገኝቷል፡፡

**የወጪ ሂሳብ፤**

3. በሰኔ/2011 በጀት ዓመት መጨረሻ በወጪ ሂሳብ ሪፖርትና በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መካከል ብር 1,893,606.78 ልዩነት ተገኝቷል፡፡
4. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት የስልክ አገልግሎት ክፍያ ብር 660,491.89 ተገኝቷል፡፡
5. በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ በድምሩ ብር 1,693,095.32 ተገኝቷል፡፡

6. በአምቦ ከተማ ለተደረገ ስልጠና ለሰልጣኞች የተከፈለ በሚል በስልጠና ላልቆዩባቸው ቀናት አለአግባብ የውሎ አበል ክፍያ በመፈፀሙ በድምሩ ብር 410,024.00 በብልጫ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል።
7. በመ/ቤቱ ስም ላልተመዘገበ የሞባይል ስልክ የአገልግሎት ክፍያ በድምሩ ብር 5,274.17 ተፈጽሞ ተገኝቷል
8. በናሙና ከተመረጡ የወጪ ማስመስከሪያዎች ውስጥ ማስረጃ ባለመቅረቡ በድምሩ ብር 47,724,348.01 ወጪ የተደረገባቸው የክፍያ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

9. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ በድምሩ ብር 8,853,648.00 ተገኝቷል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 አስከ 9 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተከፈለውን ወጪና የበጀት አጠቃቀም በትክክል ያሳያሉ ብሎ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤**

10. በኃላፊ ሳይፈቀድ በድምሩ ብር 11,497.70 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።
11. በአንድ የግዥ መጠየቂያ ሁለት ግዜ የተፈፀመ ግዥ በድምሩ ብር 5,999.54 ተገኝቷል።

**በጀት፤**

12. የመደበኛ በጀት ብር 188,982,202.76 ሥራ ላይ ያልዋለ መገኘቱ ታውቋል።

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

**ንብረት፤**

- ብር 51,308.49 ዋጋ ያላቸው እቃዎች በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ወጪ ሳይደረጉ ለተጠቃሚዎች የተሰጡ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ብዛታቸውን ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

**<u>የተሸከርካሪዎች አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፡</u>**

- ብዛታቸው አስራ ሶስት (13) በግቢውና በጋራዥ ውስጥ በቀላልና ከባድ ብልሽት ከሶስት ወር እስከ ሁለት ዓመት ያህል ያለአገልግሎት የቆሙ መኖራቸው ተረጋግጧል፡

ከሠላምታ ጋር

----------------------